ብፁዓን እለ የአምሩከ ወእለ ሥርግዋን በፍቅርከ

ወንሕነኒ ሕይወቶ ነሐዩ በእንቲአከ




ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ

፹ኛ ዓመት የልደት በዓል መታሰቢያ

በተለይ የወጣ

ሐምሌ ፲፮ ቀን ፲፱፻፷፬ ዓ. ም

ቍጥር ፪

www.ethiopianorthodox.org

# አዲስ ሕይወት

ይህ መጽሔት ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሰማንያኛ ዓመት ለሚከበረው በዓላ ልደት መታሰቢያ በተለይ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ የታሪክና የሥነ ጽሑፍ ማደራጃ ዋና መምሪያ ተዘጋጀ ።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በነገሡ በ፵፪ ዓመት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ የኢትዮጵያ ፓትርያርክ በሆኑ በሁለተኛው ዓመት

[illegible] ታተመ ።

www.ethiopianorthodox.org



ማኅቶተ ቤተ ክርስቲያን ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ፤

www.ethiopianorthodox.org



የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል መርዕድ አዝማች
አስፋ ወሰን ኃይለ ሥላሴ ፤

www.ethiopianorthodox.org



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ።

www.ethiopianorthodox.org



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ
ለመጽሔቱ መክፈቻ ቀጥሎ ያለውን ቃለ በረከት ሰጥተዋል ።

www.ethiopianorthodox.org

## የቅዱስነታቸው ቃለ በረከት ፡

ልደት ቀዳማዊ ተዐውቀ በደኃራዊ ልደት፡ቀዳማዊ ልደት፡በኋለኛው ልደት ታወቀ/ጊዜ የሥራ መምሪያ እንደመሆኑ መጠን ቃላትን በየመልኩ እንዲጠቀሱ ያደርጋቸዋል ። መስታወት በፊቱ ያለውን እንደሚቀበል ቃላትም ጊዜ የሚሰጣቸውን መልክ ሊቀበሉ ይችላሉ፡ከዚህ በፊት ለሃይማኖት ትምህርት ሲሠራበት የኖረው ጥቅስ ዛሬ የታሪክ ገጽ ይዞ ተገኝቷል ። ሰው ሁለት ልደታት አሉት፡አንዱ ከአባቱና ከእናቱ በሥጋ መወለድ፡ሁለተኛው በሥራ ከታሪክ መወለድ ነው፡ይህ የግብር ልደት አንድ የሚባለው በሥራ ሲጠቃለል ነው እንጂ ቁጥር ሊወስነው አይችልም ፡ በዚህ ምክንያት ወአነ ዮም ወለድኩከ ያለውን ቃል መጽሐፍ ለትንሣኤ አድርጎት እናገኛለን፡ቃሎት የጊዜን የሥራ መልክ ሊቀበሉ ይችላሉ ያልንበትና ይህን ሃይማኖታዊ ጥቅስ ከታሪክ ያወራረስንበት ምክንያቱ ይህ ነው፡ይህ ግርማዊ ልደት የዛሬ ሰማንያ ዓመት የታወቀው በአካባቢው ብቻ ነበር፡ዛሬ ግን የሚታወቀው፡በክብር የሚታሰበውና የሚከበረው በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ግዛቶች ሳይወሰን በመላው የአፍሪቃ አህጉርና በዓለም ልዩ ልዩ የኢትዮጵያ ወዳጅ ሀገሮችም ጭምር ነው ።—

ግርማዊ ጃንሆይ በሥራ ከታሪክ እንደገና በመወለዳቸው ይህ ታሪካዊ ልደት ጥንታዊውን ልደት በመላው ዓለም እንደገና በገናንነት እንዲታወቅ ስለአደረገው በዚህም አባታቸው ዳዊት ወይጽናሕ ምስለ ፀሐይ ያለው ቃሉ ፍጻሜነትን ስለአገኘ ቀዳማዊ ልደት በኋለኛው ልደት ታወቀ ተባለ፡መጽሐፍ፡የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግ ለዘለዓለም ይኖራል ።—

እግዚአብሔርን የሚፈራ ትእዛዙንም አጥብቆ የሚወድ ምስጉን ነው ፡ ሥራው ክብር ጌጥ ነው፤ ጽድቁ ለዘለዓለም ይኖራል፡ሥልጣኑ በክብር ከፍ ከፍ ይላል ብሏል ፡ ይህ ለግርማዊ ጃንሆይ ተፈጽሞ እናየዋለን ስማቸው በሥጋዊና በመንፈሳዊ የታሪክ ሠሌዳ ተጽፎ ሥራቸውም ለሀገራቸውና ለቤተ ክርስቲያናቸው ክብር ጌጥ ሆኖ እንመለከታለን፡በዚህም የሚሰማን መንፈሳዊ ደስታ ፍጹም ነው፡ስለዚህም እግዚአብሔር ክብሩን ጸጋውን እየሰጠና እያደሰ እንዲያኖርልን እንለምነዋለን ።—

እግዚአብሔር ዘኵሎ ትእኅዝ ንስዕለከ ወናስተበቊዐከ በእንተ መፍቀሬ እግዚአብሔር ንጉሥነ ኃይለ ሥላሴ ወባቊዐ ሎቱ ጸግዎ አግርር ፀሮ አሕዛበ ዘመንገለ ዐረፍቱ ወተናገር ጽድቀ ውስተ ልቡ በእንተ ቅድስት ቤተ ክርስቲያንከ ፍጡነ ይርከቦ ሣህልከ እግዚኦ ሀቦ ዘእንበለ ስሕተት ይዕቀብ ልቡና ዘሃይማኖት ውስተ ሥነ አምልኮትከ በአሐዱ ወልድከ ዘቦቱ ለከ ምስሌሁ ወምስለ ቅዱስ መንፈስ ስብሐት ወእኂዝ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም አሜን ።—

# መቅድም

ይህ መጽሐፍ፤ ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሰማንያኛ ዓመት ለሚከበረው በዓለ ልደት መታሰቢያ ነው፤ ይህ የሰማንያኛ ዓመት በዓለ ልደት መታሰቢያ በሀገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን፤ ከሀገር ውጭም በመላ አፍሪቃ አገሮች እንዲከበር በሞርኮ ራባት ላይ የተሰበሰበው የአፍሪቃ መሪዎች ጉባኤ ወስኗል። ይህም አስደናቂ ክብር የጃንሆይን ከፍተኛ ሥራ የሚመሰክር ከመሆኑም በላይ ኩራትነቱ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን መሆኑ ግልጽ ነው።

ከዚህም በቀር እግዚአብሐር ኢየሱስ ክርስቶስ ለሀገራችን ቸርነቱን ዘወትር ያላቋረጠ፥ የማያቋርጥ መሆኑን፤ ከክብር ወደ ክብር የሚመራት እሱ መሆኑን ያረጋግጣል፡

ይህ በዓል ፥ ብዙ ትዝታ ያሳድርብናል፤ መቸም ልደት ማለት፤ ሰው የሰውነት ክብሩን ወደሚያገኝበት፥ ወይም ወደማያገኝበት ዓለም የሚገባበት በር ማለት ነው፤ ሰውን ፍጹም ሰው ሊያደርገው የሚችል ተፈጥሮው ብቻ ሳይሆን ሥራው ጭምር ነው፤ ያለዚያ ከእንስሳት የሚሻልበት ምክንያት አይኖርም፤ ከሥራም ሥራ ይለያል፤ ሰዎች ዕውቀታቸውን፥ ጉልበታቸውን፥ ገንዘባቸውን ብቻ አምነው የሚሠሩት ሥራ ለጊዜው በክረምት ምክንያት እንደተነሣ ልዩ ልዩ ዓይነት ሣርና ቅጠል ከፍ አድርጎ ያሳያቸው ቢመስልም ፥ቆይቶ የገናንነታቸው ትምክሕታቸው፥ ኩራታቸው ሁሉ እንዳልነበረ ይሆናል፥ አንዳንዶች በዓለምም እንኳ ቢሆን የሚቀራቸው ክፉ ስም ብቻ ነው፤ አንዳንዶችም የሐውልት መታሰቢያ ቢኖራቸው በመሬት መናወጥ፥ በአደገኛ ጦርነት፥ ይህን በመሰለ ልዩ ልዩ ከባድ ምክንያት ወድቆ ተሰባብሮ ከመሬት በታች ይውላል።

እግዚአብሔርን አጋዥ አድርጎ በሃይማኖት የሚሠራ ሥራ ግን፤ በወዲህም ዓለም በወዲያኛውም ዓለም ሰውን የታሪክ፤ የክብር፥ የስም ባለቤት ያደርገዋል፥ የማይጠፋ አክሊል ያቀዳጀዋል፥ የማይጠፋ የማይደመሰስ መታሰቢያም ከእግዚአብሔር ይሰጠዋል፥ ኖኅ ፥ መልከ ጼዴቅ፥ አብርሃም፥ ኢዮብ፥ ሙሴ፥ ዳዊት እነዚህና እነሱን የመሳሰሉት ሁሉ ከእግዚአብሔር ያገኙት የክብር መታሰቢያ ዓለማውያን ምድራውያን ባለታሪኮች ካገኙት ሁሉ እጅግ ከፍ ያለ ነው።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከሥራ ሥራ መርጠው ለይተው የሚሠሩ፥ እግዚአብሔርን አጋዥ አድርገው ሥራቸውን የሚያከናውኑ፤ ሃይማኖታዊ መሪ በመሆናቸው በእግዚአብሔር ፈቃድ ከፍ ያለ ስም አግኝተዋል፤ ይኸውም የሰላም መሪ መባል ነው፤ እግዚአብሔር ምንጊዜም ዓለምን ያለመሪ አልተወውም፤ ግን መሪዎች የግል ፍላጎታቸውን ስለሚከተሉና ዓላማቸውን ከእግዚአብሔር ገለል ስለሚያደርጉ ሰላምን በመፈለግና በመሻት ፈንታ ለጦርነት ስለሚያደሉ የሥራቸው ውጤት የተዛነፈ ይሆናል፤ ግርማዊነታቸው ግን እግዚአብሔር የሰጣቸውን የሕግ መምሪያ ስለሚከተሉ፤ ከጦርነት ይልቅ ለሰላም ስለሚያደሉ በኃይል ከሚሠራ ሥራ ይልቅ በሰላም የሚሠራ ሥራ እጽፍ ድርብ ውጤት አለው ብለው ስለሚያምኑ በዚህም ዓይነት መምሪያ ሥራቸውን ስለሚያከናውኑና ሥራውም ከፍ ያለ ዋጋ ያለው ሆኖ ስለተገኘ ገና በዚህ ዓለም ሳሉ የሰላም መሪ፥ የሃይማኖት ጋሻ መባልን አገኙ።



የሥራቸውንም ፍሬ ራሳቸው ለማየት በቁ የታሪካቸው ፍሬዎች ተብለው ሊጠቀሱ ከሚገባቸውም ዋና ዋናዎቹ አዲሲቱ ኢትዮጵያና አዲሲቱ አፍሪቃ፤ የኢትዮጵያ ሙሉ ዕድገትና የአፍሪቃ አንድነት ድርጅት የምሥራቅ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ የኢትዮጵያ መንፈሳዊ መብት ፍጹምነት ናቸው። በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች ጃንሆይ ፍጹም ባለታሪክ መሆናቸው ተረግጋጦአል፤ በጃንንሆይ ሥራ ፍጹም ኩራት ከሚሰማቸው አንዷቱ በመንፈስ ልደት እናታቸው የሆነችውና በመሪነታቸው የማይረሳ ውለታ የፈጸሙላት፥ በጸሎተ ሃይማኖት ደግሞ የምታገለግላቸው ወልድ ዋሕድ ዘሀሎ ውስተ ሕፅነ አቡሁ ውእቱ ነገረነ በሚለው ዓላማ የጸናችው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ናት፤ በዓለ ልደታቸውን በፍጹም ልብ ስታከብር ከፍ ያለ መንፈሳዊ ደስታ ይሰማታል፥ ስለዚህም ይህን መጽሐፍ የልደት ገጸ በረከት አድርጋ ታቀርባለች።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን፥
የታሪክና የሥነ ጽሑፍ ድርጅት ዋና መምሪያ።



www.ethiopianorthodox.org

እኛም በወገናችን ይህችን የፍቅር መዛሪያ በፍጹም ጸሎታችን እንድትበረታ የማድረጋችንን እርግጥነቷን ታውቃላችሁ ። ስለዚህ ምክንያት ያማርኛን ቋንቋ በመንፈሳዊ ተማሪ ቤታችን አግብተን የሚያስተምሩንን መምህራን ከኢትዮጵያ አምጥተናል ።—

ከዚህ አስቀድሞ በዳግማዊ ምኒልክ ጊዜ ጀምሮ እስካሁን በኢትዮጵያ ልጆቻችሁን የሚያስተምሩ ግብፃውያን አሉና ፣ አሁንም አገራችሁ ከፍ ከፍ እያለና እየተሻሻለ እንዲሔድ ሌሎችም ቢያስፈልጓችሁ የግብፅ ወንድሞቻችሁ እንዲረዱዋችሁና የፈለጋችሁትን ሁሉ ደስታን በተመላ ልባቸው እንዲፈጽሙላችሁ የተሰናዱ ናቸው ።—

ዋና ለማስታወቅ የምንፈልገው ጎረቤት የሆነ ሕዝብ በወንድምነቱና ጥልቅ በሆነ ፍቅሩ ሀብትና በረከት ይመኝላችኋልና ከዚህ ሕዝብ የምትፈልጉትን ወንድም ከወንድሙ ለመጠየቅ እንደሚገባው እንድትጠያየቁ ይገባችኋል ።—

ዕድሜ ለግርማዊ ንግሥተ ነገሥታት ዘወዲቱና ፣ ዕድሜ ለግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ፣ ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር ፣ ብለን ለሕዝቡ ሁሉ ጤናና ሀብት እንዲሰጥና ከዚህም ያባትነት መገብኘት የተነሣ የቤተ ክርስቲያን ክብረት እየተሻሻለ እንዲሔድና የሁለቱም ሕዝብ የፍቅር ማሠሪያቸው እንዲበረታ ኢየሱስ ክርስቶስን እንለምናለን አሜን ። —

ከዚህ በኋላ የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት አቡነ ቄርሎስ ፤ አቡነ ዮሐንስ ወደኢትዮጵያ ስለ መምጣታቸው ደስታቸውን ለመግለጽ ሲሉ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል ተናገሩ ።—

ያቡነ ቄርሎስ ንግግር

ብፁዕ አባታችን የእስክንድርያ የኖባ ያምስቱ አህጉርና የኢትዮጵያ መንግሥት ፓትሪያርክ ዘነበረ በመንበረ ማርቆስ ወንጌላዊ ብፁዕ እምብፁዓን አባታችን አቡነ ዮሐንስ ሆይ ፤

ልቤን ያለመጠን ደስታ የሞላው ፣ አካሌንም ሁሉ ይባቤ የከበበው ሆኜ በሐዋርያ ጌትነትዎ ፊት ቁሜ በተለየ ሰውነቴ ላባትነትዎ እንዳንድ ልጅዎ ሆኜ ስለ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሁሉ ብፁዕነትዎን ለማመስገን ለኢትዮጵያ እልቅናዋ የኔ ስለሆነ ምትክ ሆኜ ለብፁዕነትዎ በጣሙን ጥልቅ የሆነ ምስጋናዬን አቀርባለሁ ። ይህችንም ሥልጣን በመጀመሪያ ያገኘኋት ከቤተ ክርስቲያን ጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስ ፈቃድ ሆኖ ነው ።

ሁለተኛም የተቀደሰውን እጅዎን በኔ ላይ አድርገው እኔን ለዚህ ሥልጣን አብቅተው ቀድሰው ስለባረኩኝ ለብፁዕነትዎና በተዋሕዶ ለማይለዩ ልጆችዎ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ካህናትና ኤጲስ ቆጶሳት ከላይ እንደተነገረው ሁሉ ይህችን መልካም ጊዜ ያማረች የተካከለች በተዋሕዶ ሃይማኖት ክብራ የጸናች በብፁዕናዎ መምጣት ምክንያት በከበረችው ቀን ለሐዋርያ ጌትነትዎ ደስታዬንና ምስጋናዬን አቀርባለሁ ።

ደግሞም ይህንኑ ለጌትነትዎ ምስጋና ማቅረቤ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በመላው ደስታዋ ፍጹም ስለሆነ በታላቅ ሐሳብና በፍቅር በይባቤ የሃይማኖቷ ጌታ ዋና ጠባቂዋን የጳጳስዋን ሊቀ ጳጳስ ንጹሐ ንጹሐኑን በምስርና በሱዳን ባምስቱ አህጉር ምዕራብና በኢትዮጵያ በቅዱስ ማርቆስ መንበርና በፓትሪያርክ ብፁዕ አቡነ ዮሐንስነትዎ ስል ምስጋናዬን አቀርባለሁ ፣



ስለዚህም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ሁሉ በመላ ወደተባረከው የኢ. ትዮጵያ መንግሥት መምጣትዎ ያለመጠን ደስ አላቸው ። ስለዚህም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሁሉ ፣ ወደ ኢትዮጵያ በመምጣትዎ በጣሙን የበዛ ደስታ ደስ ይበላት ።

ይህም መምጣትዎ ሃይማኖትን የሚያጸና ያባትነት ትምህርት ማቅናት ዋና ትልቅ ምክር ይገኝበታልና ። ይህንም ማዕርግ ሊቀ ጳጳሱ ዋናው ፓትሪያርክ ወደሀገሯ መምጣቱን ኢትዮጵያ ተከልክላ ብዙ ትውልድና ዘመን ይህነን ተስፋ ሳታገኝ ትኖር ነበር።

አሁን ግን የኢትዮጵያ መንግሥት በተለየ ደስታ ደስ ይበላት ፣ ንጹሕ በሆነ በሐዋርያነትዎ መንፈስ ቅዱስ የተጠመቀች ትሁን ፣ የኢትዮጵያ መንግሥት በተለየ ቤተ ክርስቲያንዋም በመላ የሰላም አስተማሪዋ በተዋሕዶ ያከበራት የሃይማኖት አባቷ መጥቶላት እንደምን ደስ አይላትም ።

አሁንም ብፁዕ አባታችን ሆይ፤ መንግሥቱንና ቤተ ክርስቲያኑን ባንድነት ባዲስ ሰላምና ባዲስ ኪዳን አስማምተው የሚያስተምሩ ነዎ ። የተባረኩት የተቀደሱት የሰላም እግሮችዎ እዚህ ከረገጡ በኋላ ፣ በርእሰ ሰላም በታላቁ በጠባቂዎች ጠባቂ በጌታችን ባንዱ በኢየሱስ ክርስቶስ ኃይል የሁለቱን የመንግሥቱን የካህናቱን ሰላምነት የሚያቆይ ይሁን ።

የኢትዮጵያ አገር ሁሉ ዛሬ ትዘምራለች ። ከዳዊት መዝሙር ጋር እንዲህ ስትል በኢትዮጵያ አየር ላይ ያለ ሰውም፤ እንስሳውም ቡቃያውም አትክልቱም በውሆችም ውስጥ ያለ ተንቀሳቃሽ ሁሉ በያይነቱ ምስጋና ያቀርባሉ ። የአዕዋፍም ዓይነቶች በየዛፉና በየተራራው ላይ ሁነው ስለደስታው የምስጋና ቃል ይሰጣሉ ። ወደፊትም ለሚመጣው ደስታ ቅኔ ምክንያት፤ ስለዚህም ከሰው ልጅ ደስታን ይካፈላሉና ።

ደግሞም ስለመድኃኒታችን አለቃ ምትክ ሆነው ሕዝባቸውን ሊያስታውሱ፤ የሃማኖትን ዓምድ ሊያፀኑ አስበው ስለመጡ ይላልና እሱም እውነተኛው ጠባቂ ነው። በበር የሚገባ ፣ መንጎቹም ቃሉን ያውቁታልና ይከተሉትማል በጎቹ ናቸውና ። ይህም ከሆነ አሁን እኔ ይገባኛል ፍጡራንን ሁሉ ባንድነት ለመጥራት ፣ ሰውንም እንስሳውንም ፤ ተራራውንም በዚህ በተናገርሁት ሁሉ የቅዱስ እግዚአብሔርን ስም እንዲያመሰግን ፣ ይህም ፍጡር ሁሉ በቃል ባይናገር ምሳሌው ለሐዋርያው ጌትነትዎ እንኳን ደኅና ገቡ እያለ ምስጋና ያቀርባል ።

ደግሞ አሁን እኔ ለራሴ ለቅዱስነትዎ እስከዚህ ድረስ እንኳን ደኅና ገቡ ማለቴን በታላቅ ደስታ ክብርና ምስጋና አቀርባለሁ ። ደግሞም እንደዚሁ ሁሉ ምስጋናዬን ለሁለቱ ክቡራን ከብፁዕነትዎ ጋራ ለመጡ በቤተ ክርስቲያን ሥራ ሁሉ ለረዱዎ ለአቡነ ሉቃስና ለአቡነ ዮሳብ የከበረ ምስጋናዬን አቀርባለሁ ።

እነሱም በዚህች በተባረከችው ጉዞ ከቅዱስነትዎ ጋራ ስለመጡ ክብር ይገባቸዋል ። የመንፈስ ቅዱስ ርኅራኄ በነሱ ብፁዕነት አድሯልና ፣ ደግሞም እንደዚሁ ሁሉ ከፓትሪያርክነትዎ ጋር ለመጡት ለተባረኩት ልጆችዎ ሁሉ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

ደግሞም በመንገድና በውሀ ላይ ደክመው ከእስክንድርያ ከሐዋርያው መንበር ከማዕርግ ሹመትዎ ላይ ተነሥተው ወደዚህች እሩቅ ወደሆነች አገር መምጣትዎ እጅግ አድርጎ ደስ ያሰኛል ።



www.ethiopianorthodox.org

እዚህ ላይ፤ ስለ ሥርዓተ ንግሥ አንዳንድ ነገሮችን እንመለከታለን፣ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት፤ ንጉሠ ነገሥት ተብሎ በኢትዮጵያ የንጉሠ ነገሥት መንግሥት ዙፋን ላይ ሲቀመጥ በሚፈጸመው ሥርዓተ ንግሥ ውስጥ የሃይማኖትን ዕድገት የተከተሉ ልዩ ልዩ ሥርዓቶች አሉበት፤ (ሀ) ኢትዮጵያ ሕገ ኦሪትን ከመቀበሏ በፊት በሕገ ልቡና ሳለች፤ ነገሥታቱ ልብሰ ፀሐይ፣ ወይም አርዕድ፣ አንቀጥቅጥ ፣ የሚባለውን ልብሰ መንግሥታቸውን ለብሰው፣ ዘውድ ደፍተው፣ በትረ መንግሥት ይዘው ሉል ጨብጠው ይነግሡ ነበር ። ከጦር መሣሪያዎቻቸውም ጕላ ብለው የሚታዩት ጦርና ቀስት ናቸው፣ልብሰ መንግሥቱ የግዛታቸውን ስፋትና ግርማቸውን ገናናነታቸውን፣ በትረ መንግሥቱ ተከላካይነታቸውን ጥበቃቸውን፣ ሉሉ በአንድ አምላክ ማመናቸውን፤ ጦሩ የጦር መሪ መሆናቸውን ያሳያል፣ እንዲያውም ልብሰ መንግሥታቸውልብሰ ፀሐይ መባሉ የፀሐይ ብርሃን ለሁሉ በሁሉ እንደሆነ፣ ሥልጣነ መንግሥትም በሁሉ ላይ የተዘረጋ፣ ሁሉን ለመጠበቅ የቆመ ከመሆኑም በላይ በሕገ ልቡና የነበሩ አማኞች አምላክን ለመፈለግ ፀሐይን ከፍተኛ ምልክት ያደርጉ ነበር፣ ይህንንም የአብርሃም ታሪክ ያስረዳል ።

ኢትዮጵያም በዚያን ጊዜ ከአበው ቃል በቃል በተቀበለችው ትምህርት፤ ሰማይን ምድርን በውስጥዋ ያሉትን ሁሉ የፈጠረውን አምላክ ታመልከው ነበርና በዚህ ምክንያት ነው፤ አንዳንድ ጸሐፊዎች ግን ይህን ተመርኩዘው ፀሐይን ታመልክ ነበር ብለው ጽፈዋል፣ አላመለከችም፣ ይህንንም የሕዝቡ ልማድ ሊያስረዳ ይችላል፣ የሥነ ፍጥረት ትምህርት ያልተማረውን ማንኛውንም ኢትዮጵያዊ ስለ ፀሐይ ቢጠይቁት፤ ፀሐይ ዋጋ የማይከፈልባት የእግዚአብሔር ገንዘብ ናት ይላል እንጂ፤ ፀሐይ አምላክ ናት አይልም፤ የንጉሥ ሥልጣን ለሁሉ መሆኑንም ሲያስረዳ፤ የንጉሥ ሞት የፀሐይ ዕርበት አንድ ነውና ፀሐዩን ንጉሥ አሰንብትልን እያለ ይጸልያል፣ ይህም ከአበው የወረደ ትምህርት ነው

(ለ) ኢትዮጵያ፤ ሃይማኖተ ኦሪትን ከተቀበለች በኋላ፤ ነገሥታቶችዋ የቀድሞውን የክብር ምልክቶች አሳይተው በሕገ መጽሐፍ የሚነግሡ ሆነዋል፣ በዚህም ጊዜ ባለ ኦሪ ማገዝ ቀለበት አድርገው ፣ ሰይፍ ታጥቀው፤ ቅብዐ መንግሥት ተቀብተው፤ ዳግም ሕግ ተነቦላቸው፤ ሃይማኖትንና አገርን አጣምረው ሊጠብቁ በእግዚአብሔር ስም እየማሉ የሚነግሡ ሆነዋል ። ሰይፉ፤ ሥልጣናቸው፤ ሥጋዊና መንፈሳዊ ኃይል ያለበት መሆኑን፤ ቀለበቱ ሃይማኖታቸውን፣ ቅብዐ መንግሥቱ መንፈስ ረድኤት የሚሰጣቸው መሆኑን ያመለክታል ። የንግሡ ሥነ ሥርዐት የመንግሥተ እስራኤልን ጠባይ ስለያዘ ሳሙኤል፣ ሳኦል በመንግሥቱ የሚፈጽመውን ሁሉ አስቀድሞ ለሕዝቡ እንደ አወጀላቸው በዚህም ንጉሠ ነገሥቱ ሕዝቡን ሊያስተዳድር በት ያሰበው ዓዋጅ ይገለጥበታል፣ እንዲሁም ሳሙኤል ዳዊትን በወንድሞቹ መካከል ቅብዐ መንግሥት እንደቀባው ፤ሊቀ ካህናቱ ንጉሠ ነገሥቱን በሕዝቡ መካከል ቀብቶ ያነግሠዋል፤ ንጉሠ ነገሥቱም እንደ እግዚአብሔር ትእዛዝ ሕዝቡን እንዲመራ፣ ሥራውን እንዲሠራ በኦሪት ዘዳግም ምዕራፍ ፲፯ ከቁጥር ፲፬ እስከ ፳ ያለውን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ካህኑ አንብቦ በእግዚአብሔር ስም ያምለዋል፤ ከዚህ በኋላ መዘምራኑ ከዳዊት መዝሙር አርባ አራተኛውን መዝሙር እየዘመሩ ሥርዐቱ ይፈጸማል ።

(ሐ) ኢትዮጵያ፣ ሃይማኖተ ወንጌልን ከተቀበለች በኋላ በአእምሮ እያደገች እንደ መሔዱዋ መጠን የክርስትና ሥርዓት ተጨምሮበታል፣ ሥርዓቱ የቀድሞውን መልኩን ሳይለቅ በወንጌል ሥርዓት ተደግፎአል፣ በኦሪት ሌዋውያን ካህናት ፈንታ፤ ወንጌላውያን ካህናት፤ በሊቀ ካህናቱ ፈንታ፤ ሊቀ ጳጳሳት፣ በቤተ መቅደስ ፈንታ ቤተ ክርስቲያን፣ በመሥዋዕተ ኦሪት ፈንታ መሥዋዕተ ወንጌል ተተክተዋል፤ ጸሎቱ፤ብሉይ ኪዳንን፣ ሐዲስ ኪዳንን ያስተባበረ፣ ምክሩ በትንቢተ ነቢያት ላይ ስብከተ ሐዋርያትን ያጣመረ ስለሆነ፣ በመዝሙረ ዳዊት ላይ ከሐዋርያ መልእክታት ከግብረ ሐዋርያትና ከወንጌል ቃላት ምክር ይሰጣሉ፣ ከሐዋርያት አስተብቁዖታት አንዳንድ ጸሎታት ይጸልያሉ፣ በዚህ ዓይነት ሥርዓቱ ሲፈጸም ኖሮአል ።

በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሥርዓተ ንግሥ ግን፤ ሥርዓቱ ተብራርቶ ተጣርቶ ሕጋዊ መልክ ይዞ ተፈጽሟል፤ ከዚህ ቀጥሎ በሥርዓተ ንግሡ ላይ የተፈጸመውን ሁሉ ከተላለፈው ዜና እናያለን ።

ሬታና ቤተሰቡ
ቤተ መጻሕፍት

ክፍል ፱

## ሥርዓተ ንግሥ

ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ከረፋና የስድስቱ ወር መዋዕለ ኃዘን ከተፈጸመ በኋላ በሰባተኛው ወር የንጉሠ ነገሥቱና የእቴጌዪቱ ዘውዳቸው፣ሌላውም የንግሡ መሣሪያና ዕቃ ሁሉ በቤተ መንግሥቱ ግቢ ውስጥ ወደ ቤተ ክርስቲያን ወደ ዳግማዊ ምኒልክ መታሰቢያ ቤት፣ ገብቶ ከያውራጃው የመጡ ።

፩ኛ ጳጳሳት ።
፪ኛ ቆሞሳት ።
፫ኛ መነኰሳት ።

ተሰብስበው ሁለት ሱባዔ ያህል የሚገባውን ጸሎት ከጸለዩበት በኋላ ለበዓለ ንግሡ ሰባት ቀን ሲቀረው፣ ከዳግማዊ ምኒልክ መታሰቢያ ቤት ወደ መናገሻ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ሔዱ ።

በዚሁም ቀን በጅሮንዱ ለንጉሠ ነገሥቱና ለእቴጌዪቱ የተሰናዳውን የሥርዓተ ንግሥ መሣሪያ ሁሉ ለትልልቅ ሹሞች አሲዞ ወደ መናገሻው ሥፍራ ሲሔድ የክብር ዘበኞች በፊትና በኋላ፣ በቀኝና በግራ አጅበው አብረውት ሔዱ ።

ዘውዱ ወደ መናገሻ በሔደበት ቀን፤ የዳግማዊ ምኒልክ መታሰቢያ ካህናት ያለዘቡት ።

ግሥ

እመሰ ጾምከ ወጸለይከ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ትጸውር ባዝግና ወርቅ ውስተ ክሣድከ ፣ አክሊለ ክብር ዲበ ርእስከ ።
በጽርሐ ቅድሳቱ ለምኒልክ ዕበ ይኤምኁከ ጳጳሳት ።

ዘውዱና የንጉሡ ዕቃ ሁሉ፣ ወደ መናገሻው ሲገባ የመናገሻ (ገነተ ጽጌ) ካህናት በአለቃቸው አስተናባሪነት በቤተ ክርስቲያኑ ቅጽር ግቢ ተሰብስበው ። ንሴብሖ ለእግዚአብሔር ስቡሐ ዘተሰብሐ እያሉ ተቀበሉ ።

www.ethiopianorthodox.org

አቤቱ ቅዱስ አብ ሆይ ፣ የክብር ፣ የምስጋናም ዘውድ አድርግላቸው አሜን ።— ጸሎቱንም ሲጨርሱ ይህን የደስታና የክብር ዘውድ ይቀበሉ ፣ ይህን የወርቅ ዘውድ እንደጫኑ ፣ እግዚአብሔር በልብዎ እርሱን የሚፈሩበት ፣ ንጉሠ ነገሥቱን የሚያከብሩ በት ዘውድ ይጫንልዎ ብለው ዘውዱን ጫኑላቸው ።—

እቴጌዪቱም ዘውዱን ከጫኑ በኋላ ፣ ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ቀርበው ባንገት እጅ ነሥ ተው በወርቅ ወንበራቸው ላይ ተቀመጡ ፣ ከዚህ በኋላ በዚያው ሥፍራ የተሰበሰቡት ሕዝብ ሁሉ ይበጅ ያድርግ እያሉ በየቆሙበት ሆነው እጅ ነሡ ።—

ሴቶች ወይዛዝርም እልል አሉ ። ካህናቱም አክሊለ ተቀጸላ ታንሶሱ የሚለውን ወርበው በከበሮና በጸናጽል ደስታቸውን ገለጹ ።

ከዚህ ቀጥለው መዘምራኑ ወይሰግዳ ሎቱ አዋልደ ጢሮስ በአምኃ ብለው ወያ በውእዎን ውስተ ጽርሐ ንጉሥ ከሚለው ሲደርሱ ዝም አሉ ።—

በዚያም ጊዜ የመንግሥት ዘር የሆኑ አራት ወይዛዝር ለእቴጌዪቱ በአንገት እጅ ከነሡ በኋላ ፣ አክሊላቸውን እያደረጉ በእቴጌዪቱ ኋላ በተዘጋጀላቸው ወንበር ተቀመጡ

ከዚህ በኋላ አሥሉስ ቅዱስ መሐረነ ተብሎ ዲያቆኑ እስመ በጸሕኮ በበረከት ሠናይ ወአንበርከ አክሊለ ዲበ ርእሱ ዘእምዕንቍ ክቡር ፣

ሐይወ ሰአለከ ወሀብኮ ብሎ ሰበከ ።

ቀጥሎም የኢትዮጵያ ደቡብ ጳጳስ ፣ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ወንጌል አነበቡ ።

ወንጌል ዘማቴዎስ ፤ ወእምዝ ሖሩ ፈሪሳውያን ወተማከሩ ከመ ያስሕትዎ በቃሉ ወፈነዉ ኀቤሁ አርዳኢሆሙ ምስለ ሰብአ ሄሮድስ ወይቤልዎ ሊቅ ነአምር ከመ ራትዕ አንተ ወበጽድቅ ትሜህር ፍኖተ እግዚአብሔር ወኢተሐሰብ መነሂ ወኢታደሉ ለገጸ ሰብእ ንግረነከ እንከ ዘይረትዕ ይከውንሁ ውሂበ ጸባሕተ ዲናር ለንጉሥ ወሚመ ኢይ ከውንኑ ወአእመሮሙ እግዚእ ኢየሱስ እከዮሙ ወይቤሎሙ ምንተ ታሜክሩኒ መደል ዋን አርእዩኒ አላ ደዲናሩ ወአምጽኡ ሎቱ ዲናረ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ ዘመኑ ዝንቱ መልክኡ ወጽሕፈቱ ወይቤልዎ ዘነጋሢ ወይቤሎሙ ሀቡ ዘነጋሢ ለነጋሢ ወዘእግዚአብሔር ለእግዚአብሔር ፣

ወሰሚያሙ አንከሩ ወኀደግዎ ወሖሩ ። ማቴ ፳፪፥ ቁ ፲፭—፳፪ ።

የወንጌሉንም ቃል የኢትዮጵያ ምዕራብ ጳጳስ ባጭሩ አድርገው በአማርኛ ተረጎሙ ከዚህም በኋላ ሊቀ ጳጳሱ ፣ የፓትሪያርኩን የአቡነ ዮሐንስን የቡራኬ ቃል ባረብኛ ከተናገሩ በኋላ አስተርጓሚው ቀጥሎ እንደተጻፈው በአማርኛ አነበበ ።—

መልእክተ በረከት

በስም ፲፱ኛ በቅዱስ ማርቆስ ወንበር ለተቀመጡት ፩፻፲፫ኛ ፓፓና ፓትሪያርክ ዮሐንስ።

እምቅድመ ዓለም በጌትነቱ ፣ በአምላክነቱ ብቻውን የሆነ ፤ በአካል ሦስት የሆነ፤ የውነተኛ አምላክ የአብ ፣ የወልድ ፤ የመንፈስ ቅዱስ የሥሉስ ቅዱስ በረከት ምሉዕነ ትና የእግዚአብሔር ረድኤት በላዩኛይቱ ጽዮን ለንጹሐን ሐዋርያት የተሰጠ ሰላሙ ይህ ሁሉ በፍጹም እግዚአብሔርን በሚፈሩ ልዕልናና ክብራቸው ከፍ ከፍ ባለ በእግ ዚአብሔር ወዳጅ በንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ላይ ይደሩ ።—



የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የኢትዮጵያን መንግሥት ዘውድ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ የጫኑ የእውነተኛዪቱን እምነት አደራ ጠባቂ የኦርቶዶክሳውያንን ቤተ ክር ስቲያን ክብር በመጠበቅ የቆሙ ፣ ልዑል እግዚአብሔር የግርማዊነታቸውን ሰውነት በአምላክነቱ አጥር ውስጥ ይጠብቅ ። የሰማይም መላእክት መልካም ሰውነታቸውን ዙሪያውን ከበው ይጠብቁ ፣ በኀነትና ፈሪሃ እግዚአብሔር ፍርድ ማስተካከል እምነት በመንግሥታቸው ና በሀገራቸው የተዘረጋ ይሁን ። ልዑል እግዚአብሔር የተባረኩትን ግርማዊት መነንን በቀኝ እጁ ይጠብቅ ። የተከበሩትን ሀብታሞቹን ልጆቻቸውን ይጠ ብቅ ። በአባታቸው ጥላ ውስጥ ክብርን ፣ ሀብትን ይጨምርላቸው ። ሁለተኛውንም ደስ የሚያሰኘውን ረዥሙን የጤና ዕድሜ ይስጣቸው ፤ ራሶችና ሚኒስትሮችን የመንግሥ ቱን ሹማምንቶች በታመነው ግርማዊነታቸው ጥላ ሥር ዕድሜያቸውን አቆይቶት ደስ ታና ጤና ፣ ሰላምና ክብር ይስጣቸው ። የመንፈስ ቅዱስ በረከት የኢትዮጵያን መንግሥት በመላ ያደረሰ ይሁን ። በግርማዊ ሰውነታቸው ዕድሜ ከመርዘም ጋራ ፣ ኢትዮጵያንም ስጦታዋንና ክብሯን ለዘለዓለም ያቆያት ። በቅድስት ንጽሕት እመቤታችን በድንግል ማርያም አማላጅነት በእስክንድርያ ሐዋርያ በቅዱስ ማርቆስ ፣ በብፁዓን ሐዋርያቶች በንጹሓን ቅዱሳኖች ፣ በባለአክሊሎች ሰማዕታቶች ፣ በእውነተኛዎች ጻድቃኖች አማላ ጅነት አሜን ።—

ንጉሠ ነገሥት ሆይ

የእግዚአብሔር ጸጋ ለርስዎ ይሁን ።

የጌታችን የአምላካችን የኢየሱስ ክርስቶስ የአባታችን የእግዚአብሔር አብ ሰላም ለርስዎ ይሁን ። እኔም በየጊዜው ሁሉ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ፤ በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት አልጋ ላይ የማውጣትን ጸጋ እግዚአብሔር ስለሰጠዎ ልባችንንም ደስታ የመ ላው ይባቤ የከበበው ነገር ይህ ነው ። እኛንም ወንድሞቻችንንም ጳጳሳትን ፣ ኤጲስ ቆጶ ሳትን ፣ የቤተ ክስርቲያናትንም ሰዎች ማኅበሩን የግብፃውያንንም ኦርቶዶክሳውያን ሕዝብ በምድረ ግብፅ እጅግ ደስ አለን ።—

ስለዚህ እኛም ደግሞ ይኸንን ዋና ታላቅ ከፍ ማለትን ከሰማን ቀን ጀምሮ ስለና ንተ እንጸልያለን ፣ እንለምናለንም ።

ከመንፈስ ቅዱስም ዕውቀትን ፣ ጥበብን አእምሮን ሁሉ በፈቃዱ እንዲመላችሁ ፣ ለእግዚአብሔር እንደሚገባው በሚወደው ሁሉ አካሔድ እንድትሔዱ በጎ ሥራችሁ ሁሉ ያፈራ ሆኖ ፣ የእግዚአብሔር ዕውቀት አድሮባችሁ ሁሉን የሚችል አምላክ ጸጋውን ከሱ ዘንድ እንዲሰጣችሁ ፤ የተቀደሰውን ስሙን ታመሰግኑ ዘንድ ፤ እኔም በሥጋ ከናንተ የራቅሁ ብሆን እንኳ በመንፈስ ከናንተ ጋራ ነኝ ። ደስ እያለኝ ያካሔዳችሁን መልካም ነት በኢየሱስ ክርስቶስ የእምነታችሁን ጽናት እመለከታለሁ።በዳዊት በነቢዩ የተነገረው የእግዚአብሔር እጅ ፣ በንጉሥ ልብ ላይ ነው ፣ እንዳለው ልባችሁን የገዛት ይሁን ። ዋና የሆነች መንግሥታችሁን የምታዘጋጁበትን ጥበቡንና በረከቱን እግዚአብሔር ሰላሙን ያሳድርባችሁ።—

እኔም ደግሞ ለግብፃውያን ኦርቶዶክሳውያን ቤተ ክርስቲያን ፍቅራችሁ ለዘለዓ ለሙ እየጨመረና እየበረታ መሔዱን በውነት አውቃለሁ ። ደግሞም ወደፊት በመጨ



www.ethiopianorthodox.org

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የእነዚህ ብፁዓን አበው አየራዊ ጉዞ ተቃንቶ የሐዱብ ትም አሳብ ተከናውኖ በደኅና ደርሰው እንዲመለሱ በኀዘንና በጸሎት ሰነበተች ።—

ምዕራፍ ፲ ክፍል ፲፯ ።

ሢመተ ጳጳሳት ኢትዮጵያውያን፤

በአላፉት ዓመታት በልዩ ልዩ ምክንያት መሰናክል አግኝቶት የነበረውን የሁለቱን ቤተ ክርስቲያኖች ጉዳይ የግርማዊነታቸው ትጋትና ትዕግሥት መልካም ፍጻሜ እንዲያገኝ አድርጎ የስምምነቱ መፈጸም ከተረጋገጠ በኋላ አምስቱ ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት ብፁዕ እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ፤ መምህር ገሪማና ሊቀ ሥልጣናት መልእክቱ፤ መምህር ዘፈረ ብርሃንና መምህር ጌታሁን ሐምሌ ፲፯ ቀን ፲፱፻፵ ዓ ም ዓርብ ከጧቱ በ፩ ሰዓት ከ፲ ደቂቃ ከአዲስ አበባ ተነሥተው በኢትዮጵያ ያየር መንገድ ተጉዘው በ፲፩ ሰዓት ካይሮ ገቡ ።—

የአየሩም መንገድ በአሥመብና በሉክሶር ላይ ነበር፤ ጳጳሳቱ ካይሮ ፋሩክ ፊልድ ላይ ከአይሮፕላን ሲወርዱ በካይሮ ያሉት የኢትዮጵያ ሚኒስትር ክቡር ፊታውራሪ ታፈሰ፤ ክቡር ሳባ ሐበሽ ፓሻና ቆሞስ ኢብራሂም ሉቃስ፤ የፓትሪያርኩ መልእክተኞችና ጳጳሳት ሌሎችም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ወዳጆች ደስ በሚያሰኝ አኳኋን ተቀበሏቸው ።—

ኢትዮጵያውያኑ ጳጳሳት በተቀባዮቻቸው ታጅበው ካይሮ ከተማ እንደገቡ በመጀመሪያ ወደ በትረ ካናው ሔደው ለብፁዕ ፓትሪያርኩ ለአቡነ ዮሳብ ሰላምታ አቀረቡ፤ ፓትሪያርኩም በደስታ ተቀብለው ጥቂት ጊዜ ካነጋገሩዋቸው በኋላ ተሰናብተው በኢትዮጵያ ሊጋሲዎን ወደ ተዘጋጀው ሥፍራ ሔዱ ።—

ብፁዕ እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስና ብላታ መርስዔ ኀዘን በዚሁ ቀን ወደማታ ወደ አብዲን ቤተ መንግሥት ሔደው በጐብኝዎች መዝገብ ላይ ስማቸውን ጽፈው ተመለሱ ።—

የፓትሪያርኩ ሽልማት፤

የኢትዮጵያ ነገሥታት ለሃይማኖት አባቶቻቸው ለእስክንድርያ ፓትሪያርኮች ሽልማት መስጠት ልማዳቸው ነው፤

እንደዚሁ ሁሉ፤ግርማዊ ንጉሠ ነገሥታችን ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ለብፁዕ ፓትሪያርክ ለአቡነ ዮሳብ በጣም ደስ የሚያሰኝ ሽልማት የወርቅ ላንቃና የሥላሴን ኮርዶን ኒሻን ልከውላቸው ነበርና፤ ክቡር ፊታውራሪ ታፈሰና ብላታ መርስዔ ኀዘን ይኸንኑ ሽልማት ለማስረከብ፤ ሐምሌ ፲፯ ቅዳሜ በ፱ ሰዓት በቀጠሮ ወደበትረ ካናው ሔዱ ።—
በትረ ካናው በግብፅና በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ አጊጦ ነበር ። ፓትሪያርኩም





በ፲፱፻፵ ዓ/ ም ሐምሌ ፲፰ ቀን የተሾሙት አምስቱ ኢትዮጵያውያን ብፁዓን ጳጳሳት ።

www.ethiopianorthodox.org

ፈሳዊ ሥጋዊ ሕይወት ታድሶ በዓለ ዕረፍቱ ከዳግማዊ በዓለ ሢመተ ጳጳሳት ተባብሮ ሲከበር ማየት የድንቅ ድንቅ ነበር ፤ ከጳጳሳቱም አምስቱ አዲሶች ሲሆኑ ስድስተኛው አብረዋቸው የተሾሙት አቡነ ይስሐቅ በመሆናቸው የቤተ ክርስቲያን ሕይወት ትናንትናም ዛሬም የማይለወጥ መሆኑ ታይቶአል ሐምሌ ፳፫ ቀንም እንደገና በብዙ ሺህ የሚቆጠር ሕዝብ በተሰበሰበበት ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መሳፍንትን መኳንንትን አስከትለው በተገኙበት በመናገሻ ቅዱስ ጊዮርጊስ ከፍ ያለ በዓል ተደርጎአል። ከየአድባራቱ የመጡ ካህናት ከሌሊቱ ጀምረው ማኅሌቱን ሲያከናውኑ ዋሉ በአራት ሰዓት ተኩል ብፁዓን ጳጳሳት በክብር ታጅበው ከመናገሻ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ደረሱ ፤ ወደ ቤተ መቅደሱም ገብተው ጸሎተ ሕሊና ሲያደርሱ እንደ ቆዩ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ልዑል አልጋ ወራሽን አስከትለው በሞተር ቢስክሌተኞች ታጅበው ከቤተ ክርስቲያን ደረሱ ፤ ወደ ውስጥም ገብተው ጸሎተ ሕሊና ካደረሱ በኋላ ታቦቱ ወጥቶ ዑደት ተደረገ ፤ በዑደቱ ላይም ህየንተ አበውኪ ተወልዱ ለኪ ደቂቅ ወትሠይሚዮሙ መላእክተ ለኩሉ ምድር ወይዘክሩ ስመኪ በኵሉ ትውልደ ትውልድ የሚለው ምስባክ ተሰበከና ከዮሐንስ ወንጌል ም ፲ ተነበበ ። ከዑደቱ ፍጻሜ በኋላም ጸሎተ ቅዳሴው በብፁዓን ጳጳሳት ተከናውኖ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ወደ ቤተ መንግሥታቸው ፤ ብፁዓን ጳጳሳትም ወደ ማረፊያቸው ሲመለሱ የበዓሉ ፍጻሜ ሆነ ።—

ምዕራፍ ፲፩ ክፍል ፲፰ ።

ሊቀ ጵጵስና ፤

ምንም እንኳ ሊቀ ጵጵስና ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት ቢሾሙም ፣ የእስክንድርያው ፓትሪያርክ የወደደውን ይሹምላቸው እንጂ የኢትዮጵያ ሰዎች ከአዋቂዎቻቸው ሊቀ ጳጳሳት አይሹሙ ፤ ያውም ቢሆን በስም ሊቀ ጳጳሳት በመባል ብቻ ይክበር እንጂ ጳጳሳትን ሊያጳጵስ አይገባውም የሚለው ኀደብ እስከ ተጣሰና አሳዛኙ ሰው ሠራሹ ግንብ እስከ ፈረሰ ድረስ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ መብት ጉዳይለሚሰማ ፤ ለሚያይ ፣ ለሚያስተውል ሕሊና ዕረፍት የማይሰጥ ስለሆነ ሰላማዊው መሪ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የሰላም ትግላቸውን አላቋረጡም ።

ስለዚህም ጉዳዩ በውይይት ቆይቶ የኢትዮጵያው ሊቀ ጳጳሳት ግብጻዊው አቡነ ቄርሎስ ባሉበት መብታቸው ተጠብቆላቸው ቆይተው ጥቅምት ፲፪ ቀን ፲፱፻፵፫ ዓ ም ካረፉ በኋላ በዚሁ ዓ ም ጥር ፮ ቀን ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ ካይሮ በሚገኘውበቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን ከእስክንድርያው ፓትሪያርክ ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ዮሳብ መዓርገ ሊቀ ጵጵስና ተቀብለው የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት ሆኑ ።

በዚህ ጊዜ ጃንሆይ የፈጸሙት መንፈሳዊ ተግባር ለሁለቱ ሀገሮች ለእስክንድርያና ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታላቅ ውለታ ሠርቶአል ፣ እስክንድርያና ኢትዮጵያ ባልተመጣጠነ የሥልጣን ይዞታ ሺ ስድስት መቶ ዓመት ሲኖሩ እያደር እየሠፋ የሄደ ቁስል ታይቶአል ፤ ኢትዮጵያውያን ቅዱስ ፍሬ ምናጦስን መርጠው ለሥልጣነ ክህነት ወደ እስክንድርያ ሲልኩት በፈቃዳቸው ነው እንጂ ሌላ ምክንያት አልነበረበትም ፤ ቅዱስ ፍሬ ምናጦስም ወደ ኢትዮጵያ እንደተመለሰ ሊቀ ካህናቱ እንበረምን ሕዝበ ቀድስ ብሎ በመ





ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ ሊቀ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ
፲፱፻፵፫ ዓ. ም. ጥር ፮ ቀን

www.ethiopianorthodox.org

በእኔም ውስጥ የሚገኙ ጳጳሳት ቀሳውስትና ዲያቆናትም እንደ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ሕግና ሥርዓት ቤተ ክርስቲያንን እንዲጠብቁ ለግርማዊነትዎ በሕግ ለታወቁ ወራሲያን መንግሥትዎ ታማኞች ሆነው እንዲያገለግሉ አደርጋለሁ ።

ታኅሣሥ ፴ ቀን ፲፱፻፵፫

አባ ባስልዮስ እጨጌ ወጳጳስ ።

እኛ ባለንበት በዚህ ቃል —ኪዳን ገብተው ሲፈርሙ ተመልክተናል ።

አባ ቴዎፍሎስ ጳጳስ ዘሐረር
አባ ያዕቆብ ጳጳስ ዘለቀምት
አባ ጢሞቴዎስ ዘይርጋ ዓለም
አባ ይስሐቅ ዘሰሜን ኢትዮጵያ

ግርማዊነታቸውም ቀጥሎ የተመለከተውን ቃል ተናገሩ ።

የግርማዊነታቸው ቃል ፡

በቤተ ክርስቲያን ሕግ መሠረት የተደረገውን የሊቀ ጵጵስና ምርጫ ተመልክተን ለቤተ ክህነታችንና ለቤተ መንግሥታችን ፍጹም መሆንዎን እየገለጹ ፡ በፊታችን ያቀረቡትን ቃል ኪዳን ተቀብለን የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ እንዲሆኑ ፈቅደናል ።—

ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ሃይማኖታችን የምትስፋፋበትን የእግዚአብሔር ቤተ ሰብእ ምእመናን የሚበዙትን መንፈሳዊ ተግባር ለመፈጸም እግዚአብሔር እንዲረዳዎት ከልባችን እንመኝልዎታለን ።—

የቃል ኪዳኑ ሥርዓት ከተፈጸመ በኋላም ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ለእስክንድርያ ፓትሪያርክ ከዚህ በታች የተጻፈውን መልእክት አስተላለፉ ።—

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ስለ ሊቀ ጳጳሳት ቅብዓት
ለፓትሪያርኩ ለብፁዕ አቡነ ዮሳብ የጻፉት ቃል
ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ
ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።

ለብፁዕ አቡነ ዮሳብ ፪ኛ

ቅዱስ ቡራኬዎ ይድረስን ዘንድ እየለመን ሰላምታችንን እናቀርባለን ። የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ሥርዓተ ቅብዓት ጥር ፯ ቀን ፲፱፻፵፫ ዓ ም ካይሮ ላይ እንዲፈጸም የብፁዕነትዎ መልካም ፈቃድ መሆኑን የካይሮ ሚኒስትራችን ስላስታወቀን ፤ በቤተ ክርስቲያናችን ሕግ መሠረት ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ ሊቀ ጳጳስ ሆነው የተመረጡበትን ተመልክተን ፣ እኛም የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ እንዲሆኑ ሹመታቸውን ፈቅደናል ። ስለዚህም ሥርዓተ ቅብዓቱ እንዲፈጸምላቸው ልከናቸዋል ።—

ሁለቱን ቤተ ክርስቲያኖች በፍቅር አስተሳስሮ ለመኖር ሁላችንም የደከምንበት ጉዳይ በዘመነ መንግሥታችንና ብፁዕነትዎ በመንበረ ማርቆስ በተቀመጡበት ዘመን ፍጻሜ በማግኘቱ ፤ ይህን ዕድል ለፈቀደልን ለእግዚአብሔር ምስጋና እያቀረብን የተሰማንን ታላቅ ደስታ ለብፁዕነትዎ እንገልጻለን ።—



ለብፁዕነትዎ ረጅም ዕድሜና መልካም ጤና ልዑል እግዚአብሔር እንዲሰጥዎ ከልባችን እንመኛለን ።—

ታኅሣሥ ሠላሳቀን ሺህ ዘጠኝ መቶ አርባ ሦስትዓመተ ምሕረት፡ በነገሥንበሐያኛው ዓመት በአዲስ አበባ ቤተ መንግሥታችን ተጻፈ ።—

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ።—

በዚህ በግርማዊነታቸው መልእክት መሠረት ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ ሊቀ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ጥር ፮ ቀን ፲፱፻፵፫ ዓ ም ወደካይሮ ሔዱ ፤ በዚያም የኢትዮጵያ አምባሳደርና የግብጽ ቤተ ክርስቲያን መልእክተኞች በታላቅ ክብር ተቀበሏቸው ።

ጥር ፯ ቀን እሑድ ፲፱፻፵፫ ዓ ም ሥርዓተ ሢመተ ሊቀ ጵጵስናው በካይሮ ባለው በቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን በብፁዕ አቡነ ዮሳብ ፪ኛ የእስክንድርያ ፓፓና ፓትሪያርክ እጅ ተፈጽሞ ፤ ጥር ፲፮ ቀን ፲፱፻፵፫ ዓ ም ተመልሰው አዲስ አበባ ገቡ ።

በዚህም ቀን በታላቁ ቤተ መንግሥት ከፍ ያለ አቀባበል ተደርጓል ፤ ይህም ዕለት እንደሌሎቹ ዕለታት ሁሉ የሥራ ፍሬያቸውን ምርት ለሚያዩት ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴና የሥራ ፍሬያቸውን በዙራት ተቀብላ መሥዋዕተ ሰብሐት አድርጋ ወደ ልዑል እግዚአብሔር ለምታቀርበው ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዕለተ ፍሥሐ ነበር ።

ከዚህም በቀር ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲጠመቅ ለክርስቲያን አዲስ ሕይወት የተመሠረተበት ረቂቅ ምሥጢር የተገለጠበት በመሆኑ ሀብተ ወልድና የሚገኝበት ይህ መንፈሳዊ መብት በዚሁ ቀን ለኢትዮጵያ ከልዑል እግዚአብሔር በመሰጠቱ ቤተ ክርስቲያን እኩት እግዚአብሔር በእንተ ጸጋሁ እንተ ኢትተረጎም እያለች ታመሰግነዋለች ። እዚህ ላይ ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ ሊቀ ጳጳስት ዘኢትዮጵያ በግርማዊ ንጉሠ ነገሥትና በግርማዊት እቴጌ ፊት ያደረጉትን ንግግር እንመለከታለን ።—

የብፁዕ አባታችን ንግግር ፡

ጃንሆይ ፡

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ዕድል በሊቀ ጵጵስና ማዕርግ እድገት አግኝቶ ለዚሁም ዕድል ቀዳማዊ ሆኜ በመገኘቴ ከሁሉ አስቀድሞ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ ።

ግርማዊ ሆይ ፡

በክርስቶስ ክርስቲያን የመባልን ዕድል ቀደም ብላ የወሰደችው ኢትዮጵያ የሃይማኖትና የምግባር ባለቤት በመሆኗ መንፈሳዊና ሥጋዊ ሀብትን አጣምራ ይዛ ስትሠራበት እስከዚህ ዘመን ደርሳለች ።

የመንፈስ ብርታት ለሥጋ ደካማነት ኃይልን ስለሚሰጠው መንፈሳዊ ሀብትና ሥጋዊ ሀብት ተደጋጋፊዎች ሆነው ይኖራሉ ። ኢትዮጵያ በፊት በኦሪት በኋላም በወንጌል የእግዚአብሔርን አምልኮ ተቀብላ ስታምን ቤተ መንግሥቱና ቤተ ክህነቱ ባንድ ልቡና በአንድ ፈቃድ ተቀብለውታል ።—



www.ethiopianorthodox.org

ለነፃዪቱ አገሬ ነፃ ቤተ ክርስቲያን ያስፈልጋታል በማለት አስቦና አርቆ ተመልክቶ ግርማዊነትዎ ከዛሬ ሐያ ሦስት ዓመት በፊት የጣለው መሠረት ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በዓለም ላይ ለታወቀው ክብርና ስምዋ የተገባውን የተቀደሰውን የነፃነት መብት አስገኙላት ።—

ማናቸውንም ሥራ ለመሥራት ሲታሰብ ሁለት ችግሮች መኖራቸው የታወቀ ነው። እነሱም መጀመርና መጨረስ ናቸው ። እነዚህ ሁለቱ ሀብቶች ዕድልዎ ሆነው ለግርማዊነትዎ ስለተሰጡ በዘመንዎ ተጀምሮ መልካም ፍጻሜን ያላገኘ አንድም ትልቅ ሥራ የለም ።—

ግርማዊ ሆይ ፤

ጥንታዊ ወጉንና ሥርዓቱን ጠብቆ የኖረውን ሕዝብዎን የአዲሱ ዘመን ሥልጣኔ ያስገኘው ጥቅም ተካፋይ ለማድረግ ኑሮውን በሀብት ለማደርጀትና በጥበብ ለማደላደል ከሁሉ የተሻለ ዘዴ ትምህርትን ማስፋፋት መሆኑን በማሰብ የግርማዊነትዎ ትጋት ያደራጃቸው የተማሩ ልጆች ለኢትዮጵያ ቀዋሚ ዕድል ለመስጠት በአሁኑ ጊዜ በሰፊው ለሚደከምበት ሥራ ዋና ረዳት ለመሆን ችለዋል ።—

ማንኛውንም የተገኘውን ጥበብና ዕውቀት ጠቃሚ የሚያደርገው እግዚአብሔርን መፍራት መሆኑ በሕፃናት አእምሮ እንዲቀረጽ ለማድረግ በየጊዜው ግርማዊነትዎ የሚሰጠው ምክር የሕሊና ምስክርና ወቃሽ ሆኖ ሁሉንም ወደ ቁም ነገር ስለ ሚመራቸው እርምጃቸው የቀናውን መንገድ ተከትሏል ።—

« ሰው ፈጣሪውን ከአመነ ሥልጣኔው የደኅንነት ሥልጣኔ ሊሆንለት ይችላል » ሲል ግርማዊነትዎ የተናገረው ቃል ሃይማኖትና ምግባር የሌለበት ሥልጣኔ አጥፊ መሆኑን አስረድቷል ።—

ይህም እየተደጋገመ በሥራ የተመሰከረ ዘለዓለማዊ ታሪክ ነው ፤ የሰው ልጅ በዕውቀቱና በጥበቡ በዙሪያው ያለውን ነገር ሁሉ ለማወቅና ለመመርመር ችሏል ። ራሱን ግን ፤ ለመመርመርና ለማወቅ የሚችለው በሃይማኖትና በምግባር ብቻ ነው ። የሰው ልጅ ከበጎ ምግባር ከራቀ በኋላ ጥበቡም ዕውቀቱም ሀብቱም ከጭንቅ ሊያድነው እንደማይችል የዛሬው ሁኔታ ያስረዳል ።—

የአገርን ነፃነትና ክብርን ፤ ሕይወትን ከሁሉ አብልጦ የሚያስበው ግርማዊነትዎ የሕዝብ የሥልጣኔ እድገት ዘላቂ ጥቅም ሊሰጥ የሚችለው ከመንፈሱ እድገት ጋር ትይዩ ሆኖ ሲሔድ መሆኑን በማስተዋል በዚህ ታላቅ በሆነው ታሪካዊ ዘመን ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ያስገኙላት መብት የዕድልን በር ከፋች ነው ።—

እንዲሁም በግርማዊነትዎ ትዕግሥትና እውቀት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ጋር ያላትን ጥንታዊ መገናኛ ሳያቋርጥ የጠየቀችውን መብት በስምምነት እንድታገኝ መደረጉ በሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት መካከል የጠበቀ ዝምድና የሚያስከትል ነው ።—

ግርማዊ ሆይ ፤

ታሪክዎን ዘወትር ከፍ ያደረገው ሁል ጊዜ ከእግዚአብሕር ቸርነትና ረድኤት በታች በመጣልና የእኔ ድካም ምንም አያደርግም ፤ ሁሉንም የሚፈጽም የእግዚአብሔር



ቸርነት ብቻ ነው በማለትዎ ነው ፤ በሥራና በድካም የተገኘ እውነተኛ ደስታ ዘላቂ ስለሆነ የግርማዊነትዎ ዕድል አያቋርጥ ። ከእግዚአብሔር ጋር የጀመረ ፤ ከእግዚአብሔር ጋር ይጨርሳል ተብሏል ። እግዚአብሔር የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን እርምጃ ያቃና ፤

ዕድሜ ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት
ዕድሜ ለግርማዊት እቴጌ
ዕድሜ ለልዑላን ንጉሣዊ ቤተ ሰብ
ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር ።—

የግርማዊነታቸው ንግግር ።

በዘመናችን ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እንዲፈጸሙ ካሰብናቸው ና ከሠራናቸው ነገሮች ከሁሉ የበለጠ አድርገን የምንቆጥረው የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት ለኢትዮጵያ የመሾሙ ጉዳይ ስለተፈጸመ ድካማችንን ለባረከ እግዚአብሔር ምስጋና እናቀርባለን ።

ይህም ዛሬ ተፈጽሞ የምናየው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ራሷን የሚያስችል ሥራ ከተጀመረበት ከብዙ ዓመታት በፊት አንስቶ ጉዳዩ እያደገ እንዲሔድና እዚህ እንዲደርስ ለማድረግ የነበረውን ድካም ያለፈበት መንገድ ስናስበው የከባድነቱ ታላቅነት የሚዘነጋ አይደለም ። አሁን ግን እግዚአብሔር የሚሠራውን ሥራ በፈቀደ ጊዜ ስለሚፈጽም ኢትዮጵያ አገራችን ነፃ ሕዝባችንና መንግሥታችን ራሷን የቻለች ቤተ ክርስቲያን እንዲኖራቸውና በዓለምም እንዲታወቅ አደረገ ።

ይህም በዘመናችን ስለተፈጸመልን እኛም ሕዝባችንም እኩል የምንኰራበት ነው ። ያለፉት አባቶቻችን ይህን ተመኙ ፤ በተስፋም ተመለከቱት ። በሃይማኖት የጸናችም ተስፋ በዘመናችን ስትፈጸም ለማየት አበቃን ።—

ብፁዕ አባታችንም ለዚህ ከፍ ላለና ለተቀደሰ ሥራ በዘመናችን ጀማሪ ለመሆን መልካሙ ዕድል ስለደረሰዎ ደስታችንን እንገልጥልዎታለን ።—

በዚህም በዛሬው ቀን የግብዕና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያኖች በበለጠ የሚከባበሩበትና የሚተማመኑበት አዲስ ዘመን ተከፈተ ።—

ይህም ይፈጸም ዘንድ ከእግዚአብሔር በተገለጠላቸው ና ብሩህ በሆነ የመግባባት መንፈስ በበኩላቸው ለረዱ በቅዱስ ማርቆስ መንበር ለተቀመጡ ለብፁዕ ዳግማዊ ዮሳብ ከፍ ያለ ምስጋናችንን እንገልጣለን ።—

በዘመናችንና በዘመናቸው ለተፈጸመው የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር መሻሻል ከዕድላችን ጋራ መግጠሙን ስናስበው ደስ ይለናል መንፈሳዊ ኃይል ከፍጥረት ሁሉ በላይ ለሆነው ለሰው ለዓለማዊና ለሰማያዊ ሕይወቱ ለሁለቱም ዓለም ጕዳና መሪው ነው ።

በመንፈሳዊ ኃይልም መሪነት ሰው የተቀደሰ ፍጥረቱ ሊደርስበትም ከሚገባው ለመድረስ ይችላል ፤ ብፁዕ አባታችንም ለዓለም ቁስል የመንፈሳዊ ኃይል መጽናኛና መዳኛ እንዲሆነው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተካፋይ ለመሆን ባለባት መጠን ከሚደርስብዎ ታላቅ ሸክም በቀር በተለየ የኢትዮጵያ ሕዝብ በመንፈሳዊ ኃይል የዚህ ዓለም



www.ethiopianorthodox.org

እንዲያተርፉ እግዚአብሔር ያዘጋጀልዎ ተክሎች ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት የዚህ ዓመት አዲስ ፍሬ ሆነው በመገኘታቸው ድካምዎን ለባረከ እግዚአብሔር ከልብ ምስጋናችንን እናቀርባለን ።

የብፁዕነታቸው ንግግር እንደተፈጸመ፤ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት መንፈሳዊ መሪ እንደመሆናቸው መጠን ፤ ለሕሊና ጠልቆ የሚሰማ መንፈሳዊ ምክር የተመላበትን ንጉሣዊ ቃል መልስ ሰጡ ።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት፤ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ወፓትርያሪክ ዘኢትዮጵያ በገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት ላደረጉት ንግግር ።

## የሰጡት መልስ ።

ብፁዕነትዎ የተናገረውን ቃል በጣም እያመሰገን ደስ ብሎን እንቀበለዋለን ። በእኛው ዕድሜና በእኛው ዘመን የሆነውን የኢትዮጵያን ታሪክ የማያውቅ ሰው የለም ።

አገራችን ከጥንት ጀምሮ ታላቅ ታሪክ ያላት አገር ነበረች ። ነገር ግን በመካከሉ ታሪኳ እንደጠፋ ያህል ተቀጥሮ ቤተ ክህነትዋ በሰው እጅ የሚተዳደር ሆኖ ነበር ።

አሁን በቅርቡ በእኛው ዘመን የዓለም አብያተ ክርስቲያኖች ስብሰባ አድርገው በሚነጋገሩበት ጊዜ ፤ አለቃዋ እያለች ጭፍራዋ አትጠራም የሚል ምክንያት በመስጠቱ፤ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በጉባኤው ውስጥ መግባት አይገባትም ስለተባለ ስለ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አለቆችዋ ግብ ጾች ተጠርተው ሲሔዱ ፡ የኛ ቤተ ክህነት ወገኖች እንደ ጭፍራ ተቆጥረው ከዚያውም ውስጥ አብሮ ለመሔድ እንኳ ሳይፈቀድላቸው ቀርቶ ነበር ።

ምንም በሌሎች ሊቃነ ጳጳሳት ባይፈጸም ፤ በዚህ ጉዳይ በዚያን ጊዜ ከልክ ያለፈ ኃዘን ገብቶን በጣም ተጸጽተንበት ነበር ።

ይህ ጸጸት ሲደርስብን ከተመለከቱት መካከል ብዙዎቹ በሞት ተለይተውን ሔደዋል ። ከቤተ ክርስቲያን በኩል ግን፡ በዚያን ጊዜ ጋዜጣ ባለማንበብና ባለመስማት ብዙ የተጸጸተ አልነበረም፤ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ግን ይህ ጸጸት የሚፋቅበትን ማሰባችንና የእግዚአብሔር ፈቃዱ እስኪሆን ድረስ መድከማችንን አላቋረጥንም ነበር ። ምስጋና ለርሱ ይሁንና አሁን ስለደረስንበት ያሰብንበትና የደከምንበት ሁሉ ተፈጽሞልናል ።

ጳጳሳት እንዲሾሙ በተጀረገበትም ጊዜ እንኳን ምእመናኑ ጳጳስ ሆነው ለመሾም ሊመረጡ ከነበሩት ፡ ለጳጳስነት መመረጥ አይገባንም ብሎ የሚከራከር አንዳንድ ሰው ነበር ። እነዚያንም ሁሉ በብዙ ችግር አስረድተን የጳጳስነት ማዕርግ በሰው እጅ ተሹሞ ክብር ማግኘት ተጀመረ ። ሁሉንም የሠራውና ያሰናዳው እግዚአብሔር ነው እንጂ ሰው አይደለም እንኳንስ ሌሎቹን ጳጳሳት ለመሾም ሥልጣን ሊሰጠው ይቅርና ለራሱም ቢሆን አንድ ኢትዮጵያዊ የጳጳስነት ማዕርግ ሊሾም አይገባውም እየተባለ የሚነገርበት ጊዜ አልፎ ከኢትዮጵያውያን መካከል ፓትሪያርክ ተሾሞ ፡ ጳጳሳትም እንዲሾሙ ተደረገ፡

ለአገራችን ለኢትዮጵያ የጥንታዊ ታሪኳ ክብር ሲመለስላት በማየታችንና የኢትዮጵያም ምእመናን ይህን ማዕርግ በማግኘታቸው እኛም በዚህ ቀንና ሰዓት የዚሁ ደስታ ተካፋይ እንድንሆን የተቀደሰ ፈቃዱ ስለሆነ ውለታው በዋጋ ሊከፈል ለማይቻለው አምላክ ምስጋናችንን እናቀርባለን ።



www.ethiopianorthodox.org



ብፁዕ አቡነ መርቆሬዎስ




ብፁዕ አቡነ ሚካኤል



ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ

www.ethiopianorthodox.org



ብፁዕ አቡነ ኤብርሃም



ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ

www.ethiopianorthodox.org

ሁሉን የሚችል እግዚአብሔር ለብፁዕነትዎ መልካም ጤንነትና የሰላም ዘመን እንዲሰጥ፣ የቤተ ክርስቲያንን ፍቅር አንድነት እንዲያጸና እንመኛለን ።—

ሰኔ አሥር ቀን አሥራ ዘጠኝ መቶ ሃምሳ አንድ ዓመተ ምሕረት በነገሥን በሐያ ዘጠኝኛው ዓመት በገነተ ልዑል ቤተ መንግሥታችን ተጻፈ ።—

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ
ንጉሠ ነገሥት

የብፁዕ አቡነ ቄርሎስ ፯ኛ መልእክት ።

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን ።

ቄርሎስ ፯ኛ
በእግዚአብሔር ጸጋ
የእስክንድርያ ፓፓና የቅዱስ ማርቆስ መንበረ ስብከት
ፓትሪያርክ፣

ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት
ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ
ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ

ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ያባታችን የእግዚአብሔር የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ፣ የመሪያችንና የአጽናኛችን የመንፈስ ቅዱስም ጸጋና ሰላም በእርስዎ ላይ ይሁን —

የቅዱስ ማርቆስ መንበር የሆነችውን የግብጽንና የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ግንኙነት ለማስተካከል በኢትዮጵያ መልእክተኞችና እኛ በሾምናቸው መልእክተኞች መካከል ጁን ፳፭ ቀን ፲፱፻፶፱ ዓ ም /፲፰ ባኡና ፲፮፻፸፭ / ሰኔ ፲፰ ቀን ፲፱፻፶፩ ዓ ም በእኛ መሪነት የተደረሰበትን ስምምነት ለግርማዊነትዎ ስንልክ ለአባታዊ ልባችን ደስታ ይሰማዋል ። ጌታችን አብያተ ክርስቲያንን በመውደዱ በመንገዳችን የነበሩትን ችግሮች ሁሉ አስወገደልን ።—

በእግዚአብሔር ጸጋ ይህን ስምምነት ደንግገን ከዛሬ ጀምሮ እንዲጸና ፈቅደን ሰጥተናል ።—

ለግርማዊነትዎና ለግርማዊት እቴጌ ረጅም ዕድሜ እንዲሰጥ፤ የተወደዱ መሳፍንቱንና ካህናቱን ሕዝቡንም ሁሉ እንዲባርክና እንዲጠብቅ፤ በአገሩም ላይ ሰላም እንዲሆን ሁሉን ወደሚችል አምላክ እንጸልያለን ።—

የእግዚአብሔር ጸጋ በእርስዎ ላይ ይሁን ።
ለዘላለም ክብር ምስጋና ይግባው አሜን ።—
ቄርሎስ ፯ኛ

የእስክንድርያው ፓፓና የቅዱስ ማርቆስ መንበረ ስብከት ፓትሪያርክ

www.ethiopianorthodox.org



ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ፣
ሰኔ ፲፱ ቀን ፲፱፻፶፩ ዓ ም ለፓትሪያርኩ የጻፉት ቃል
ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ
ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ
ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ
ለቅዱስ አቡነ ቄርሎስ ሳድሳዊ ።
የእስክንድርያ ፓፓና የመንበረ ማርቆስ ፓትሪያርክ
ካይሮ በትረካና ።—

የቅዱስነትዎ ጸሎትና ረድኤት አይለየን እያልን ሰላምታችንን እናቀርባለን ።

በመንበረ ማርቆስ ስብከት ሥር ያሉትን የግብጽንና የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ግንኙነት በሚገባ ስለማስተካከል ጉዳይ በቅዱስነትዎ መሪነት በመልክተኞቻችን መካከል ሰኔ ፲፰ ቀን ፲፱፻፶፩ ዓ ም ስምምነት መደረጉን በመግለጽና የተፈረመውን ፕሮቶኮል በማያያዝ ሰኔ ፲፰ ቀን ፲፱፻፶፩ ዓ ም የጻፉልን ደርሶናል ። ለእኛና ለልጆቻችን ለሰጡን ቡራኬና ስለ ሕዝባችን ላቀረቡት ጸሎት ምስጋናችን እንዲደርስዎ እንወዳለን ።—

የቅዱስነትዎ ብርቱ ፈቃድና መልካም አስተያየት ያስገኘው ይህ ስምምነት የቤተ ክርስቲያኖቻችንን መንፈሳዊ ግንኙነት የበለጠ የሚያጠነክረው ነው ።—

ወደዚያም ለመድረስ ሁላችንም የደከምንበትና ያሰብንበት ጉዳይ ዛሬ ከፍጻሜ ደርሶ በማየታችን በጣም ደስ ይለናል ።—

አሁን በመጀመሪያው ጊዜም የመንበረ ተክለ ሃይማኖት ወራሽ የሆኑት የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ አሁን የያዙትን መንበር እንደያዙ ሆነው «የኢትዮጵያ ፓትሪያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት» እንዲሆኑ ስለፈቀድን የፓትሪያርክነትቱን ስያሜ በቅዱስነትዎ እጅ በቡራኬ እንዲቀበሉን ልከናቸዋል።—

ሁሉን የሚችለው እግዚአብሔር ለቅዱስነትዎ መልካም ጤንነትና የሰላም ዘመን እንዲሰጥ የቤተ ክርስቲያንን ፍቅርና አንድነት እንዲያጸና እንመኛለን ።—

ሰኔ ዐሥራ ዘጠኝ ቀን ዐሥራ ዘጠኝ መቶ አምሳ አንድ ዓመተ ምሕረት ፣ በነገሥን በሐያ ዘጠኝኛው ዓመት ተጻፈ ።—

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት

ከዚሁ መላላክና መጻጻፍ በኋላ በፊት እንደጠቀስነው ጉዳዩ ፍጻሜ አግኝቶ የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ በ፲፱፻፶፩ ዓ ም ሰኔ ፳፩ ቀን በካይሮ በቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በተገኙበት በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቄርሎስ ሳድሳዊ የእስክንድርያ ፓትሪያርክ ቡራኬ የኢትዮጵያ ፓትሪያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ሆነው ተሾሙ ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳትና ፓትሪያርክ ሰኔ ፳፩ ቀን ከእኩለ ቀን በኋላ በ፲፩ ሰዓት ግብጽ ላይ በኩቤህ ቤተ መንግሥት ስለ አዲሱ ሹመታቸው በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ፊት ሥርዓተ መሐላን ሲፈጽሙ የተናገሩት ቃለ በረከት

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ ።

በግርማዊነትዎ መሪነት ሁልጊዜ ከክብር ወደ ክብር በመሸጋገር ላደገችው ለኢ

ትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ይህ የፓትሪያርክነት ማዕርግ ዛሬ ስለተፈጸመላትና ለዚሁ ማዕርግ የእኔ ደካማ ሰውነት ቀዳሚነትን ለማግኘት ስለታደለ ከሁሉ አስቀድሚ ለልዑል እግዚአብሔር ምስጋና አቀርባለሁ ።—

ወደዚህ ከፍተኛ ማዕርግ ለመድረስ ሲፈቀድልኝ ለግርማዊነትዎ ያለኝን የታማኝነት ቃል ኪዳን በፊትዎ ቆሜ ለማረጋገጥ አጋጣሚ ምክንያት አግኝቻለሁ ።—

ግርማዊነትዎ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ለማሳደግ ይህ ዛሬ የተገኘው ማዕርግ ከነመብቱ ለኢትዮጵያ እንዲሆን ባለፉት በ፴፩ ዓመታት ውስጥ ያደረገው ድካምና ትጋት ይህን ፍሬ ለማፍራት በቅቷል ። እስከ ዛሬም ድረስ ወደዚህ ግብ ለመድረስ በግርማዊነትዎ ለተደረገው ሰላማዊ ትግል መደምደሚያው ሆኗል ።—

ያንድ ነፃ መንግሥት ና ያንድ ነፃ ሕዝብ እናት መሠረታዊቱ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በመንፈሳዊ ረገድ ራስዋን ችላ የምትተዳደር እንድትሆን ግርማዊነትዎ ያደረገው ድካም ከታሪክ በላይ ስለሆነ ፤ ዘመንዎ ዘመነ ሰላም እንዲሆንና ትውልደ መንግሥትዎ እንዲባረክ እግዚኦ ሀቦ ለንጉሥ ፤ ወጽድቀከኒ ለወልደ ንጉሥ ፤ አግርር ፀሮ ታሕተ እገሪሁ ዕቀብ ንግሦ ወሠራዊቶ ለንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ እያለች ቤተ ክርስቲያን ባለማቋረጥ ወደ እግዚአብሔር ትጸልያለች ።—

ግርማዊነትዎ ምድረ ግብጽን በሚጎበኙበት በዚህ በአሁኑ ጊዜ አጋጣሚ ሆኖ በተገኙበት በመንበረ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን በቅዱስ አቡነ ቄርሎስ ሳድሳዊ የተፈጸመው ይህ የፓትሪያርክነት ሥነ በዓል ለመጪው ትውልድ መታሰቢያ ይሆን ዘንድ በቤተ ክርስቲያናችን ከፍተኛ የታሪክ ምዕራፍ የያዘ ይሆናል ። ይህንኑም ጉዳይ ወደ ፍጻሜ ለማድረስ በእግዚአብሔር መንፈስ ለተመሩትና ዕድል ላገኙት ለመንበረ ማርቆስ ፓትሪያርክ ለቅዱስ አቡነ ቄርሎስ ሳድሳዊ ከፍ ያለ ምስጋና አቀርባለሁ ።—

ልዑል እግዚአብሔር ግርማዊነትዎን በሰላምና በጤንነት ጠብቆ ለብዙ ዘመናት ያኑር ። የአብ የወልድ የመንፈስ ቅዱስ በረከትና ረድኤት በግርማዊነትዎና በግርማዊት እቴጌ ላይ ፤ በልዑል አልጋ ወራሽና በንጉሣውያን ቤተሰብ ሁሉ ላይ ይደር ። የኢትዮጵያን ሕዝብ ይባርክ ፣ ይቀድስ ፣ ኢትዮጵያ በነፃነት ትኑር ።—

### ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት የመለሱት የደስታ መግለጫ ቃል

በአፍሪካ መካከል የክርስቲያን ደሴት ሆና የኖረችው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የሚገባትን ትልቅነትና ክብር እንድታገኝ በዘመናችን ደክመንበታል ። ድካማችንን ባርኮ ይህንን ፍሬ እንዲያፈራ ላደረገልንና ኢትዮጵያዊ ፓትሪያርክ ለኢትዮጵያ የተገኘበትን ይህን ቀን ለማየት ላበቃን ለልዑል እግዚአብሔር ምስጋናችንን እናቀርባለን ።—

በሐዋርያው በቅዱስ ማርቆስ ልጆች መካከል ዛሬ የተገኘው ይህ መልካም መግባባትና መከባበር ሁለቱ አብያተ ክርስቲያንኖቻችን በመደጋገፍ የሚፈጽሙትን መንፈሳዊ አገልግሎት ከፍ የሚያደርገውና ለብዙ ፍሬ የሚያበቃው ነው ።—

ከዚህም በቀር ከሦስት መቶ ሠላሳ ዓ ም ጀምሮ እስከ ዛሬ የኖረው የሁለቱ አብያተ ክርስቲያኖች መንፈሳዊ ግንኙነት ወደፊት ጸንቶ እንዲኖር ላደረግነው ጥረት መተማመኛ የሚሆን ጽኑዕ መሠረት ነው ።—

www.ethiopianorthodox.org



ይህ ከፍተኛ ሥራ በዘመናችን ተጀምሮ በዘመናችን እንዲፈጸም ዕድል ስላገኘን ለእግዚአብሔር የምናቀርበው ምስጋና ከፍ ያለ ነው ።—

ለጉዳዩ አፈጻጸም መልካም አስተያየት ለሰጡትና በብርቱ ፈቃድ ለደከሙበት አባታችን ለእስክንድርያ ፓፓና ለመንበረ ማርቆስ ፓትሪያርክ ለቅዱስ አባ ቄርሎስ ሳድሳዊ ያለንን ታላቅ አክብሮት ስንገልጽ ደስ ይለናል ።—

የኢትዮጵያ ፓትሪያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ በኢትዮጵያ የመጀመሪያ ጊዜ ለሆነው ለዚህ ማዕርግ በቅተው ከባድ አደራ ያለበትን የፓትሪያርክነት ተግባርዎን ሲጀምሩ ሥራዎን ለማከናወን እግዚአብሔር ይርዳዎት ።—

### ምዕራፍ ፲፬ ክፍል ፳፪

### ፍጻሜ ክብር

ስለ መንፈሳዊው ሕይወት ፣ ፍቅር ፣ የሰው መንፈስ በላላበትና በደከመበት ባሁኑ ጊዜ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ለሕዝቡ የሥራ ትምህርት በመስጠት ላይ ናቸው ፤

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የኑሮ መምሪያ በማይናወጥ ዓላማ ላይ መሠረቱ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ መብት አዲስ ተክል ፣ አዲስ ሰብል እንደመሆኑ መጠን ብዙ ጥበቃ የሚያስፈልገው ሆኖአል፤ ይልቁንም የዘመኑ ትውልድ የራሱ ክብር ፣ የራሱ ሀብት አድርጎ እንዲመለከተው በጥንቃቄም እንዲጠብቀው እንዲያስብለትና እንዲቆረቆርለት ለማድረግ የሥራና የቃል ምክር የሚያሻው ሆኖአል ፣ ስለዚህም ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃ ይ ለ ሥላሴ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ሕጋዊ መብት በመስጠት ሢመተ ጳጳሳትን በከፍተኛ ደረጃ እንዲፈጸም በማድረግ ከቤተ ክርስቲያን ተገኝቶ በዓሉን በማክበር ስለበዓሉ ከፍተኛ ግብዣ በማድረግ ፣ ለክብሩ የሚያስፈልገውን ከፍተኛ ሽ ል ማ ት በመስጠት ይህን ሁሉ በመፈጸም ለተከታዩ ትውልድ የሥራ መልክ ያለው ትምህርት ሰጥተዋል ፤ ከሕይወት ክብርም የሞት ክብር ፍጹም መሆን ስለሚገባው ፤ ብፁዓን ኤጲስ ቆጶሳት ሊቃነ ጳጳሳት ፤ ይልቁንም ብፁዐን ወቅዱሳን አርእስተ ሊ ቃ ነ ጳጳሳት ከዚህ ዓለም በሞት በሚለዩበት ጊዜ ታላቅ በዓል ማድረግ ስለሚገባ ይህንንም ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት በታላቅ ሥነ ሥርዓት እንዲሠራበት አድርገው አሳይተዋል ።

የቅዱሳን የክብራቸው ፍጻሜ በሞታቸው ነው ፤ መጽሐፍ የጻድቅ ሰው ሞቱ ክቡር ነው ይላል ፣ ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረው መልካም ገድል ተጋድለው፤ ሥራቸውን ፈጽመው፣ ሃይማኖታቸውን ጠብቀው ወደ ዘለዓለም ዕረፍት የሚሄዱ ሁሉ ከእውነተኛው ፈራጅ ከኢየሱስ ክርስቶስ የጽድቅ አክሊል ይቀበላሉ ። ስለዚህም የቤተ ክርስቲያን አባቶች ከሕይወታቸው ዘመን ይልቅ ዕለተ ሞታቸው ከፍ ባለ ሥነ ሥርዓት መከበር የሚገባው ነው ፤ ሰው ሆኖ ለዘለዓለም መኖር የማይቻል ስለሆነ ፣ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ወፓትሪያርክ ዘኢትዮጵያ በዲቁና፣በምንኩስና፣ በቅስና፣በእጨጌነት፣ በጳጳስነት፣ በሊቀ ጳጳስነት፣ በፓትሪያርክነት የኢትዮጵያ ን ቤተ ክርስቲያን ና ቤተ መንግሥት ለረዥም ጊዜ በቅድስና ካገለገሉ በኋላ ጥቅምት ፪ ቀን ፲፱፻፷፫ ዓ ም

የኑሮ ደረጃ እድገት የሚረዳ እንዲሆን ማሰብ ያስፈልጋል ። ምክንያቱም የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ወደፊት በአንድ ዓላማና አስተሳሰብ እንድትመራ ሲታሰብ ፤ አሁን የሚሰጠው ርዳታ ለተለያየ የፖለቲካ ዓላማ ማስፈሪያ የሚውል ከሆነ ይህን በመሰለ ዓላማና አጭር አስተያየት መመራት ታላቁን ዓላማ የሚያቃውሰው እንዳይሆን ያሠጋል ። ማንም የእግዚአብሔር ቤተ ሰብ እንዳይለያይ ከክርስቶስና ከአባቶቻችን እንደታዘዘው በመተማመንና በፍቅር መተሳሰር ካልተሠራ በቀር አንድነትስ እንዴት ይገኛል ? ።—

የዓለም አብያተ ክርስቲያን ጉባኤ ምንም እንኳን ልማት ነክ የሆኑትን ተግባሮች በማከናወን ለብዙ የዓለም ክፍሎች ርዳታ ሲያደርግ ቢቆይም አሁን በቅርቡ ደግሞ ቤተ ክርስቲያን በልማት ተግባር በበለጠ እንድትካፈል ያቋቋመው ኮሚሽን ብዙ አላፊነትና የሥራ ክንውን የሚጠበቅበት ነው ።—

በእንጀራ ብቻ ባይኖርም ፤ ለመንፈሳዊ ኑሮም እንጀራ ማስፈለጉ አይካድም ። ስለ ዚህ የሰው ልጅ መንፈሳዊ አኗኗር ሁላችንም ከምንመኘው ከፍተኛ ደረጃ እንዲደርስ የሚደረገው ጥረት የሰብአዊ ፍጡር የኑሮ ደረጃ የሚሻሻልበትንም ተግባር የሚያጠቃልል ሊሆን ይገባል ።

ለዚሁም ከፍተኛ ተግባር ሥራ ማስኬጃ እንዲውል ከአባል አብያተ ክርስቲያናት የሚዋጣው ገንዘብ በተገቢው ሥራ ላይ ከዋለ ለቤተ ክርስቲያናችን የኅብረትና የአንድነት በር መክፈቻ የሚሆን ከፍተኛ ተግባር መፈጸሚያ ስለሚሆን ፤ በዚህ ዘመን ላለነው ክርስቲያኖች አዲስ የታሪክ ምዕራፍ መክፈቻችን ይሆናል ።—

ስለዚህ ይህ ጉዳይ አጥብቆ የሚታሰብበት ነው ፤—

የሁላችን ረዳትና መሪ ፤ ብርሃናችንም የሆነው ፈጣሪያችን ለስብሰባችሁ መልካም ፍሬ እንዲሰጣችሁ እየለመንን ፤ ዓላማችሁ የዓለም ክርስቲያኖች ከሚጠብቁት ግብ እንዲደርስ እንዲያደርግ ከልብ እንማልዳለን ብለዋል ።—

### ምዕራፍ ፲፰

### ክፍል ፳፯
### ራስን መቻል

በሀገራችን የኑሮ ሕግ ፤ ልጆች በወላጆቻቸው ቤት ካደጉ በኋላ በጋብቻ ፤ ትዳር ይጀምራሉ ፤ ጥቂት ቀንም ከወላጆቻቸው ቤት ሥራቸውን ፤ ኑሯቸውን በማስተባበር ወንዱ ልጅ ከአባቱ ጋር እየአረሰ ፤ መጠነኛ አበል እያገኘ ፤ ሚስቱም ከእናቷ ጋር የቤት ሥራ እየሠራች ከቆዩ በኋላ ጎጆ ይወጣሉ ፤ ራሳቸውን ፤ ይችላሉ ፤ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንም ከእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ጋር በመተባበር ስትሠራ ኖራ ጊዜው ሲደርስ በ፲፱፻፶፩ ዓ ም ግንቦት አንድ ቀን የሐረር ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያውያን ብቻ ተመርጠው በሕዝብ ምርጫ በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት መልካም ፈቃድ በእግዚአብሔር ቸርነት ብፁዕ ወቅዱስ ፓትረያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ተብለው በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሲሾሙና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንበር በኃይለ ሥላሴ ተካክሎ ተደላድሎ ሲቆም ጐጆ ወጣች ፤ ራሷን ቻለች ፤ እዚህ ላይ ከፍተኛ የሚያስደንቅ ነገር አለ ፤



ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ኒሻን ሲሸልሟቸው

www.ethiopianorthodox.org

